# ፈጣን ምላሽ የሚጠይቅ የኅብረት ጥሪ ፣ ተባብረን ሀገራችንን ከመቀመቅ እናውጣ!!

የህወሓት/ኢ.ህአዴግ መንግስት ሥልጣን ከጨበጠበት ከ ፩ ሺ ፱፻፰፫ ዓ. ም. (1991 እ.አ.) ጀምሮ የኢትዮጵያን ሀገራዊ ሉዓላዊነት እየሸረሸረና የሕዝቡን መብት እየረገጠ ፈላጭ ቆራጭ ሥርዓት ሆኖ መውጣቱ ዛሬ ከምንም ጊዜ የበለጠ ግልጽ ሆኗል። ያለፉት 19 ዓመታት የህወሓት/ኢ.ህአዴግ አገዛዝ ኢትዮጵያ ድንበርዋ እንዲደፈር፤ ህዝቧ በዘር እንዲለያይና እርስበርስ እንዲጣላ፤ የኢትዮጵያ መሬት በርካሽ ዋጋ ለውጭ ባለሀብቶች ተሸንሽኖ እንዲሸጥ በአንጻሩ ደግሞ በርሃብ የሚጠቃው የሚሰቃየውና የሚሞተው ሕዝብ ቁጥሩ እንዲያሻቅብ የሆነበት፤ ብልጭ ብሎ የነበረው የዴምክራሲ ጭላንጭል የጠፋበት፣ ፍትኅ ጠፍቶ ዜጎች ሲዋከቡ ሲታሰሩ ሲደበደቡ ሲገደሉ ሲሰደዱ ዘወትር የምናይበት፤ የሀገሪቱ ሃብት በጥቂቶች፣ በሥልጣን ኮርቻ ላይ በጉልበት በወጡ አምባገነኖች እየተዘረፈ መሆኑን በየዕለቱ የምናይበት ዘመን ነው። ባጭሩ ኢትዮጵያና ህዝቧ የተዋረዱበት ዘመን ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን ሁኔታ ለመለወጥና በምትኩም ሀገራዊ አንድነቱን ጠብቆ በፍትሕ በዴሞክራሲና እኩልነት ተቃቅፎና ተፋቅሮ ለመኖር ትግል እያደረገ መሆኑም አይታበልም። ለዚሁ የተቀደሰ ዓላማ ህይውታቸውን የሰጡ ፥ አካላቸው የጎደለባቸው፥ የታሰሩ፤ የተገረፉና፣ የተሠቃዩ፣ የተሰደዱ አሁንም በትግል ላይ የሚገኙ ጀግኖች መኖራቸውም የማይካድ ሐቅ ነው። ይሁን እንጂ እስከዛሬ ድረስ የሕዝቡ ትግልና ዓመጽ የተፈለገውን ያህል ውጤት ሊያስመዘግብ አልቻለም። የትግላችን ድክመት በዝርዝርና በጥልቀት መጠናት ያለበት ቢሆንም አሁን ለሁሉም ግልጽ ሆኖ የሚታየው ግን ታጋዩ ሃይል ለሁኔታው የሚስማማ የጋራ የትግል ዓላማና ስትራተጂ በማውጣት በጋራ የተቀናጀ ትግል ለማካሄድ አለመቻሉ ነው። ታጋይ ኃይሉ አንዳንድ ጊዜ በጋራ ከመታገል ይልቅ እርስበርስ ሲወንጃጀልና ሲጠላለፍ ትግሉ ውጤታማ እንዳይሆንና እንዲዳከም ማድረጉ ለሁሉም ጎልቶ የሚታይ መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ ጉዳይ ለረዥም ዓመታት ያነጋገረ ቢሆንም ከምርጫ ፪ሺ፪ ዓም(2010 እ.አ.) በኋላ በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ሁኔታ አለ የሚለው አስተሳሰብና እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ወቅታዊ አጀንዳ ሆኗል። በዚሁ መሰረትም፤ በቡድንም ይሁን በግለሰቦች

ደረጃ፤ የትግል ኃይሎችን ለማሰባሰብ እየተደረጉ ያሉ በርካታ ጥረቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ መገመት ኣያዳግትም።

እኛም ይህንን የእንሰባሰብ ጥሪ ስናቀርብ ቡድኖችን ለማበራከት ሳይሆን በግልጽ ያልውጡ ሌሎች የመሰባሰብ ሙከራዎች ካሉ ጥረታችንን አብረን ለማስተባበር ዝግጁ መሆናችንን ከወዲሁ እየገለጽን ነው ። በመቀጠልም የእኛን የእንሰባሰብ ጥሪ ይዘትና ዓላማ በሚከተለው መንገድ አቅርበናል።

የዚህ የኅብረት ምሥረታ ሥራ ጅማሮ ዋና ዓላማው ሀገራዊ ትግሉን የሚያስተባብር ጠንካራ ኅብረት ለመመሥረት እንዲቻል ተግቶ መስራት ነው። ይህን ዓላማውን ለማሳካት እንዲቻል ሁሉንም ባለጉዳዮች ማንንም ሳያገል ለኅብረቱ መጋበዝና ማሳተፍ ነው። የህወሓት/ኢህአዴግ አደገኛ አካሄድ ያሳሰባቸውና ያገሪቱ ሁኔታ እንዲለወጥ የሚሹ የሕዝባችን የተለያዩ ክፍሎች፤ በፖለቲካ ድርጅቶችና በሲቪክ ማህበሮች የተደራጁት፤ ግለሰቦችና ታዋቂ ያገር ሽማግሌዎች፤ የሃይማኖት መሪዎችን የተደራጁ ወጣቶችና ሴቶች፤ የተለያዩ የብሄረሰብ ድርጅቶችና ስብስቦች፤ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች የተሰማሩ ኢትዮጵያውያን ስለቀጣዩ ውስብስብና ባለ ብዙ-ጎን ትግል፣ ስር-ስለሰደዱት በርካታ ሀገራዊ ችግሮቻችንና ስለመፍትሄዎቹ በጥሞና የሚወያዩበትን ለተወሰኑ ቀኖች የሚካሄድ ኮንፈረንስ (ጉባዔ) በማዘጋጀት የወደፊቱን ትግል አካሄድ እንዲወስኑ ማድረግ ወይንም ማስቻል ያስፈልጋል በሚል ጽኑ ዕምነት ነው። በተያያዥም በዚህ የመሰባሰቡን እንቅስቃሴ ጀማሪ ወገን አመለካከት ጉባኤዉ ዉጤታማ የሚሆነዉ እስከዛሬ ጎድሎ የነበረውን የጋራ ዓላማና ስትራተጂ ነድፎ የሚንቀሳቀስ በሕዝቡም ዉስጥ ተዓማኒነትና መሰረት ያለዉ የተቃዋሚዎች ኅብረት ወይም በኢትዮጵያ ሀገራዊ አንድነት፣ እኩልነት እዉነተኛ ዴሞክራሲንና የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን የሚሹ ሃይሎች የሚፈጥሩት የትግል ኅብረት እዉን ሲሆን ነዉ።

ለጊዜው የመሰባሰቡ ጥረቱ እየተደረገ ያለው በሀገር ውስጥ ከመንቀሳቀስ ታግደው (ሕጋዊነት በህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ተነፍገው) ከኢትዮጵያ ዉጭ በይፋ በሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ድርጅቶችና ያልተደራጁ ዜጎች አማካይነት ቢሆንም፣ ይህንን ሁሉንም ተቃዋሚዎች በአንድ ሀገራዊ ኅብረት ወይንም ጥምረት የማሰባሰብ እንቅስቃሴ የጀመረው ወገን የሚያሰበውና የሚያቅደው ሕጋዊ የሚባሉትንም ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች ለማካተት ነው። ጉባዔው ሁሉን አቀፍ ስለሚሆን ተቃዋሚ ድርጅቶች በሙሉ ተሳታፊዎች

ይሆናሉ። አገር ቤት ውስጥ ያሉት ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች የትግል አጋሮቻችን ስለሆኑ፣ አሁን የተጫነባቸውን አስከፊ ሁኔታ በጋራ ሕዝባዊ ትግል አስወግደን አብረናቸው በሁሉም እንቅስቃሴዎች እንድንሳተፍ መንገድ መዘርጋት ይኖርበታል፣ ማዕቀቦች ሊበጠሱ ይገባልና።

በርግጥ ባሁኑ ጊዜ ብዙ ዜጎች፤ በተቃዋሚነት የተሠለፉትና ለውጥ ለማምጣት የሚታገሉት ኃይሎች ልዩነታቸዉን አቻችለዉ ወደ አንድ ጠንካራ ሀገራዊ ኅብረት፣ ቅንጅት ወይንም ጥምረት ለመሰባሰብ ባለመቻላቸዉ ተገቢ የሆነ ሕዝባዊ ቅሬታ ማሳደራቸዉ ያደባባይ ሚስጥር ነዉ። ሆኖም ግን ይህ ቅሬታና ብስጭት ደግሞ ወደ ሌላ ጽንፍ እንዳይሄድ የሕዝቡ ጥያቄ ተገቢ ምላሽ በወቅቱ ሊሰጠው ይገባል። ምላሹ ከዘገየና ስለኅብረት ጨርሶ ላለመስማት መማልና መገዘት ከተከተለ ደግሞ የህወሓት/ኢህአዴግ ዕመቃና አስከፊ ሥርዓት ባለበት እንዲቀጥል ያደርጋል። ይህ ሁኔታ ከመፈጠሩ በፊት በተገቢ አደረጃጀት፣ የትግል ስልትና ቁርጠኝነት ሊተካ ይገባዋል። ይህ የመሰባሰብ ጥሪውን እያቀረበ ያለው ወገን አዲስ ኅብረት ይፈጠር ሲል ቀደም ባሉት ሃያ (፳) ዓመታት ውስጥ ተፈጥረዉ የነበሩትንና ዛሬም ያሉትን ኅብረቶች፤ ጥንካሬና ድክመት ከትምሕርታዊነታቸዉ አኳያ የሚመረምርና ግምገማውን የሚያቀርብ የተለያየ ተመክሮ ካላቸዉ አገር ወዳዶች የተዉጣጣ ኮሚቴ በመሰየም ከዚያም ለመማር ተዘጋጅቶ ነዉ። ተመክሮዎችን በመጭመቅ ኮሚቴዉ የሚያቀርበዉ ሃሳብ በተሰባሰቡትና ወደፊትም በሚሰባሰቡት ሃይሎችና ሰፊ አባላት ተመክሮበትና ተዘክሮበት ጠቃሚና የወደፊቱን አመላካች ሃሳቦች ነጥረዉ ይወጣሉ ተብሎ ይጠበቃል። የግምገማው ጥንቅር ዝግጅትም በመገባደድ ላይ ነው።

ይህ በመሰባሰብ ላይ ያለው ወገን በኢትዮጵያ አገር ወዳዶች መካከል ያሉ የትግልና የድርጅት ስልት ልዩነቶች ኅብረትን ከመፍጠር ያግዳሉ ብሎ አያምንም። አገራችን የገጠሟት መጠነ-ሰፊ ችግሮችን መቅረፍ መጀመር የምንችለዉ በሚያስማሙን መሰረታዊ ሃሳቦች ላይ ለመነጋገር፣ ለመደማመጥ፤ ለመናበብ፤ ለመስማማት፣ አብሮ ለመሥራት እንዲሁም በወንድማማችነትና በእህትማማችነት በቅንነት ዕውቀትን፣ ተመክሮን፣ ልምድን፣ ለመለዋወጥ ስንችል ነዉ ብሎ ያምናል። የሚከተሉት አራት (፬) መሰረታዊ ዓላማዎች ይህን የመሰባሰብ ጥሪ አቅራቢ ወገን በጋራ ሊያስማሙ የቻሉና፤ አልፎ ተርፎም ሁሉንም በሀገር አንድነት የሚያምኑ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎችን ሊያሰባስቡና ሊያስማሙ ይችላሉ የሚል ከፍተኛ እምነት የተጣለባቸው የሚከተሉት ናቸው፦

፮. በኢትዮጵያ አንድነትና የግዛት ሉዓላዊነት ላይ ግልጽና የማያወላውል ጽኑ እምነት መያዝና ማሳደር

፯. በየድርጅቶች ውስጥና በምንሰባሰብበት የኅብረት ማዕቀፍ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ አሰራርን ለማስፈንና በአገራችንም የሕግ የበላይነት እንዲኖር ጸንቶ መታገል

፰. በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ምንም ዓይነት አድላዊነት እንዳይኖርና ሁሉም በሕግ ፊት እኩል ዜጎች መሆናቸውን ማመንና በተግባርም ማስረገጥ

፱. የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥትና ሥርዓት የአፈናና የጭቆና ሥርዓት በመሆኑ መለወጥና በዴሞክራሲያዊ አስተዳደር መተካት እንዳለበት ማመን

ጥሪያችን እነዚህን አራት አንኳር ሃሳቦች የሚጋሩ ዜጎችን ሁሉንም፤ በድርጅት ያልታቀፉትን፥ በድርጅት ያተሰባሰቡትን፤ በብሄር ድርጅት ውስጥ ይሁን ወይም በአገር አቀፍ(ኅብረ ብሄር) ድርጅቶች ውስጥ፤ ህወሃት/ኢህአዴግን በነፍጥ ለመጣል የተዘጋጁ ይሁኑ ወይንም በሰላማዊ መንገድ ወይንም በሁለገብ የትግል ስልት፤ሁሉንም ያጠቃልላል። ይህ ያሰብነው ለኅብረት ምሥረታ የሚያበቃ ሁሉን-አቀፍ ጉባኤ እንዲጠራና ኅብረቱም እንዲመሰረት፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እኩል ሃላፊነትና ድርሻ ስላለው ሃሳባችሁን አካፍሉን፣ እንደማመጥ፣ እንነጋገር እንላለን። ከፍ ብለው የተዘረዘሩት አንኳዋር ዓላማዎች ይበልጥ ሊሳኩ ይችላሉ ብለው የሚያምኑበትን መንገድ ለማስረዳትና ሌሎቹን የጉባዔ ተሳታፊዎችን ለማሳመን፤ በለጣቂነትም ወደ አገር-አቀፍ ውጤታማ ኅብረት ምሥረታ ለመሸጋገር ይህ አመቺ መድረክ ነው ብለን እናምናለን።

ይህም የመሰባሰብ ጥሪ አቅራቢ በራስ አነሳሽነት የተሰባሰበ ወገን እነዚህን ዓላማዎች የሚቀበሉና በእነዚህም የሚያምኑ ናቸው የሚላቸውን አገር ወዳድ ቡድኖች፣ ድርጅቶች ወይንም የተሳሰሩ/ የተጣመሩ ድርጅቶችን መጥራቱንና እንድንሰባሰብ መጎትጎቱን በቅንነትና በከፍተኛ ሀገራዊ ሃላፊነት መንፈስ ይቀጥላል። ተመሳሳይ ጥረት ከጀመሩትም ጋር በዚሁ የሀገራዊ ኅብረት ምሥረታ ተግባር ዙሪያ አብሮ ለመስራት ወስኗል።

ማስታወሻ፦ ሁለት ነገሮች እንዲጤኑ እንፈልጋለን። እንቅስቃሴው ተጀመረ እንጂ ኅብረት አልተመሠረተም፣ ስለሆነም ይህ እንቅስቃሴ ገና ድርጅታዊ ስም የለውም። ሁሉም የሀገራቸው ጉዳይ የሚያንገበግባቸው ኢትዮጵያውያንና

ኢትዮጵያውያት አብረው እንዲመክሩ ለማድረግ ነው እየተሠራ ያለው። ከሁሉም ሃሳብና ምክር እንሻለን፣ የቅን ሀገር ወዳዶችንም ተሳትፎና ድጋፍ እንፈልጋለን። በአንድነት ሀገራችንን ለመታደግ እንነሳ እንላለን።

ይህ ጥሪ የቀረበው ለኢትዮጵያ ሀገራዊ አንድነት፣ ለፍትሕና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚታገል ሀገራዊ ኅብረት በሁሉን-አቀፍ ጉባዔ አማካይነት እንዲመሠረት በራስ አነሳሽነት በመንቀሳቀስ ላይ ካሉ የሲቪክ ማኅበሮችና የፖለቲካ ድርጅቶች አሰባሰቢ ኃይል ነው ።

የመሰባሰብ ጥረቱን የጀመሩትና ሌሎችም በሂደቱ እንዲቀላቀሏቸዉና የሀገር አድኑ ትግል አካል እንዲሆኑ ጥሪ የሚያደርጉት የሚከተሉት ናቸዉ።

<u>ከፖለቲካ ድርጅቶች</u>

- የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት
- የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዲሞክራሲያዊ)

<u>ከሲቪክ፡ ሙያና የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች</u>

- የኢትዮጵያ የሲቪክ ማህበራት ስብስብ (በእንግሊዝ ሀገር)
- የኢትዮጵያ አንድነት ዳያስፖራ መድረክ
- የአንድነት የድጋፍ ኮሚቴ በብርታንያ
- ዴሞክራሲያዊ ለውጥ በኢትዮጵያ ድጋፍ ድርጅት (ኖርዌይ)
- ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ---- ድጋፍ ኮሚቴ (አዉስትራሊያ)
- ሶሴፐ ካናዳ (Soccep-Canada)

<u>ተባባሪዎች</u>

- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጉባዔ

<u>ታዋቂ ግለሰቦች፥</u>

- <u>ድጋፍ እየሰጡን ያሉ ቢኖሩም ዝርዝሩን ለጊዜው አቆይተነዋል።</u>

**አድራሻችን።**

- **ኢ--ሜይል--** consult4eth@gmail.com
- **ቴሌፎን ---**
  - **ከአውሮፓ ሲደወል** 0039/329-784-6515
  - ---**ከአሜሪካና ካናዳ** 011/39/329-784-6515